ለአቶ አክሎግ ልመንህ
አንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማኅበር ሊቀ መንበር
ጥቅምት 16/2002

ለአንተና ለቤተሰብህ፣ ለማኅበሩ አባሎች በሙሉ የማክበር ሰላምታዬን አቀርባለሁ።

በአንድነት ጉዳይ የጻፍኸውን መነሻና መድረሻ የሌለው ደብዳቤ አንብቤ አዘንሁ፤ መልስ ሳልሰጥ እስካሁን የቆየሁትም የኔም መልስ እንዳንተ ደብዳቤ ሀሳብ የሌለበት የስሜት መግለጫ እንዳይሆንብኝ ለመጠንቀቅ ብዬ ነው።

የደብዳቤህ ርእስ፡-- **መርህን እየጣሱ የመርህ ጠባቂ መሆን አይቻልም** የሚል ነው፤ በደብዳቤህ የተጠቀሱት መርሆዎች **ለሕግ መገዛት**፣ **መሪዎችን ተጠያቂ ማድረግ**፣ **በዴሞክራሲ የአብላጫ ድምፅ የሚወሰነውን መቀበል**፣ **በፓርቲ ውስጥ የሚነሡ ተቃውሞዎችን ማክበርና ማበረታታት** የሚሉ ናቸው፤ የመጨረሻውን ከየት እንዳመጣኸው ባላውቅም በተቃና መልኩ እቀበለዋለሁ፤ በተጨማሪም ብዙ ሌሎች መርሆዎች እንዳሉ የምታውቅ ይመስለኛል፤ የአንድነት መርሆዎችና ደንቦች ሁሉ በዝምአንልም ድረ-ገጽ (አንተ እንደጻፍኸው ድህረ ገጽ አይመስለኝም) ላይ ወጥተዋል፤ በመርሆዎቹና በደንቦቹ ላይ ልዩነት የሚኖረን አይመስለኝም፤ ይህ ከሆነ ከሁነቶች እንጀምር፤ የሚከተሉት ሁነቶች ብርቱካን ከታሰረች በኋላ የተከሰቱ ናቸው፤

1. ለፓርቲው ሊቀ መንበር በኤግዜኪዩቲቭ ጸሐፊነት የተቀጠረችው ወይዘሮ ሐና ያለምንም ማስጠንቀቂያና ሕጋዊ ሥርዓት በማን አለብኝነት ከሥራዋ ተባራለች፤
2. በፓርቲው ጽሕፈት ቤት በጽዳት ሠራተኛነት የተቀጠረችው ወይዘሮ ብርቄ እንዲሁ ያለምንም ማስጠንቀቂያና ሕጋዊ ሥርዓት ተባረረች፤
3. (እነዚህ የተጠቀሱት ሁለት ሠራተኞች መባረራቸው ‹‹አስተዳደራዊ እርምጃ ነው፤›› የሚል ጮሌ-መሳይ ምክንያት ተሰጥቶአል፤ ለመሆኑ ትንሽ ማሰብ የሚችል ሰው ከፖሊቲካ ውስጥ አስተዳደር ሲወጣ የሚቀረው ምንድን ነው ብሎ ራሱን መጠየቅ ያቅተዋል?)
4. የሥራ አስፈጻሚው ውስጥ ሁለት ሰዎች የተለየ አስተሳሰብና ድምፅ አሰጣጥ በማሳየታቸው ብቻ ያለምንም ሕጋዊ ሥርዓት መጀመሪያ አገዱአቸው፤ በኋላ ግን ሁለቱንም አሰወጡ፤
5. አቶ እንደሻው የመሀል ኢትዮጵያ አስተባባሪ ኮሚቴ ውስጥ በጸሐፊነት ሲሠራ ነበር፤ ፓርቲው የገንዘብ ችግር ስለገጠመው በሚል ሰበብ ኤ/ር ግዛቸው ከሥራው ሊያስነሣው ሲጽፍለት የገንዘብ ችግር ከአለ ለፓርቲዬ በነጻ የቻልሁትን ያህል አገለግላለሁ በማለት በደብዳቤ ቢመልስለትም የቢሮውን ቁልፍ ለውጦ አስወጥቶታል፤
6. እንደዚሁም አቶ አለባቸውን ከሰሜን ቀጣና፣ አቶ አስናቀን ከምዕራብ አስተባባሪ ኮሚቴ፣ አባርረዋል፤
7. በአዲስ አበባ አቶ አምበሉን ከቦሌ ክፍለ ከተማ፣ አቶ ብርሃኑንና አቶ ሰይድን ከየካ፣ አባርረዋል፤
8. አቶ ይልቃልን ከድርጅት ኮሚቴ ጸሐፊነት፣ አቶ አንተነህን ከሕዝብ ግንኙነት አስወጥተዋል።

ሌሎችንም መጨመር ይቻላል፤ ከዚያም በላይ የተለያዩ በጣም የሚያሳፍሩ ማስፈራሪያዎች ለብዙ ሰዎች ደርሰዋል፤ ከነዚህም አንዳንዶቹ በስጋት ከአገር ወጥተዋል።

ከዚያም በተጨማሪ የደመወዝ አመዳደብ በዘደቀደ የሚደረግ እንጂ ሕግንና ሥርዓትን የተከተለ አይደለም፤ አንዱን በትክክል የሚሠራውን እውነተኛ የፓርቲ አባል አስወጥቶ በሎሌ መተካት ተደጋግሞ የታየ ነው፤ ቀደም ብለው የተጠቀሱትም ሁነቶች በከፊል ማስረጃዎች ናቸው። የአንድነት ፓርቲ ለአገራቸውና ለወገናቸው ተቆርቁረው በአንድ እምነትና ዓላማ ተያይዘው የመሠረቱት ነው፤ አሁን ግን የሁለትና የሦስት ሰዎች ሎሌዎች የተጠራቀሙበትና በገንዘብ ወይም በገንዘብ ተስፋ የግለሰቦችን ፈቃድና ትእዛዝ የሚፈጽሙበት ቤት እየሆነ ነው።

እንግዲህ አንተና ከአንተ ጋር ደብዳቤውን የጻፉት ሰዎች ከላይ የተዘረዘሩትን ሁነቶች አጣርታችሁ ለማወቅ ካልቻላችሁ መረጃ ለመሰብሰብና ለማጣራት ያላችሁን ችሎታና ብቃት ያመለክታል፤ እነዚህን መረጃዎች አውቃችሁና ተገንዝባችሁ የጻፋችሁልን ከሆነ ደግሞ አስተሳሰባችሁ ከሕገ ኀልዮት የወጣና በተዛባ የስሜት ነውጥ የተለወሰ ነው ለማለት ይቻላል፤ እንዲያውም

- **በድርጅቱ የመወያያ መድረኮች ሀሳብን ማቅረብ ሲቻል**
- **በየአደባባዩና በየኤምባሲው በአሉባልታ ማሳጣት**
- **የሊቀ መንበራችንን ስም የፖሊቲካ መጠቀሚያ ለማድረግ** ።

እነዚህና ሌሎችም የስሜት ውራጆች ከየት እንደተገኙ እናውቃለን፤ ከዝምአንልም ውስጥ በየኤምባሲው የሚሯሯጡ መሆኑ ለእኔ ፍጹም አዲስ ነው፤ አታደባልቀን! ምንም የማጣራት ችግር ጉልህ ቢሆንም እንዲህ ከላይ በተጠቀሱት ውስጥ ያሉ ሙሉ ሐሰቶች ዓላማው **ልባቸው ከሚደማ** ሰዎች ይመጣሉ ብዬ ለመቀበል ያስቸግረኛል፤ የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ እንደሚሉት አይሆንም? የወዳጅነትና የጓደኝነት ስሜትንና ታማኝነትን ወደአገር ፍቅር ለመመንዘር ሲባል የሌሎችን ንጹሕ የአገር ፍቅር ጥላሸት መቀባት ተገቢም አስፈላጊም አይደለም።

በደብዳቤያችሁ ርእስ እንጀምር፤ **መርህን እየጣሱ የመርህ ጠባቂ መሆን አይቻልም**፤ እንደምታውቁት በአሜሪካ (name five የሚል አባባል አለ) አምስት ማስረጃዎችን አቅርብ እንደማለት ይመስለኛል፤ እኔ አምስት አልጠይቃችሁም፤ አንድ ይበቃኛል፤ እስቲ እኛ የጣስነውን የአንድነት መርህ አንድ ንገሩንና አስተምሩን፤ እንደማታገኙ መቶ በመቶ እርግጠኛ ነኝ!

እንደምገምተውና አንዳንዶች በጋዜጣም ጽፈው እንዳየሁት የዴሞክራሲን መርህ ጣሳችሁ የሚባል ነገር ከዚያው ከአንድነት ጽሕፈት ቤት የተነዛ ወሬ አለ፤ ለብዙኃን ድምፅ አልተገዛችሁም እንባላለን፤ እናንተም **ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በድምፅ ሲረቱ ለምን እኛ ያልነው አልሆነም በሚል ግትር አቋም** ብላችሁ የኮነናችሁን አሉባልታውን እምነታችሁ አድርጋችሁ ነው፤ ለዚህ ጉዳይ እዚሁ በጋዜጣም አንዳንድ የውጭ ራድዮኖችም ጋር ባደረግሁት ጥያቄና መልስ ያስረዳሁ ይመስለኛል፤ መቼም ይህ ዓይነቱ ነቀፌታ የሚነሣው ወይ ስለዴሞክራሲ ባልገባቸው ሰዎች፣ ወይ አውቀው ለማወናበድ በሚፈልጉ ሰዎች፣ ወይም ከአንድነት አመራር ጋር ልዩ ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ብቻ ነው፤ ዴሞክራሲ ማለት የድምፅ ብልጫ የሚመስለው ከአለ ትምህርቱን ይከልስና ያጣራ፤ በእንደዚህ ያሉ ሰዎች የዴሞክራሲ ግንዛቤ በአፍሪካም ሆነ በሌላ አህጉር የአምባገነን አገዛዝ የሚባል የለም፤ ምክንያቱም አገዛዞቹ ሁሉ (ኢትዮጵያንም ጨምሮ) በምርጫና በድምፅ ብልጫ የተሰየሙ ናቸው፤ ዴሞክራሲ ብቻም አይደሉም

ሪፐብሊክም ናቸው! እንዲህ ዓይነቱ የዴሞክራሲ ግንዛቤ ብዙ ይቀረዋል ብቻ ሳይሆን ወደዴሞክራሲ መለያ ባሕርይ አልተጠጋም፤ በአሜሪካ እየኖራችሁ በደብዳቤያችሁ ይህ መገለጡ ቦታ በመለወጥ ብቻ ሰው መማር አለመቻሉን ከማረጋገጥ በቀር ሌላ ፋይዳ የለውም።

ደብዳቤው ሌሎችም አዲስ የፖሊቲካ ግንዛቤዎችን ሊያስተምረን ይከጅላል፤ **በሀሳብ ዙሪያና በጨዋነት ከመከራከር ይልቅ የአባላትን ስም እየጠቀሱ አሉባልታንና ተራ ስድብን በየአደባባዩና በየአፍቃሬ ወያኔ ድረ ገጾች መደርደር ... የኋላ ቀር ፖሊቲካ ነው፤** ትሉናላችሁ! የደብዳቤው ጸሐፊዎች ስለዴሞክራሲ ያላቸው ግንዛቤ የተዛባ የመሆኑን ያህል ስለፖሊቲካም ያላቸው ግንዛቤ ገና ጨቅላ ነው፤ በነሱ የፖሊቲካ ግንዛቤ የግለሰብ ስም አይነሣም፤ በአሜሪካ ተቀምጠው እንደጥንቱ የነገሥታት፣ የመሳፍንትና የመኳንንት ዘመን ሴራ በሽፍንፍንና በድብቅብቆሽ፣ በሐሜትና በሹክሹክታ የፖሊቲካ ሥራ እንዲሠራ ይፈልጋሉ! ግልጽነትና ተጠያቂነት የሚባሉት የዴሞክራሲ ቁም-ነገሮችን ገድፈዋቸዋል! የተጠያቂነት ትርጉም ከግለሰብ ተነጥሎ ምን ሊሆን ነው? ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ማለት ቢቻልም አስፈላጊ አይመስለኝም።

በአለማወቅና በሐሰት ላይ የተከመረውን የስድብ ናዳቸችሁን ከጨረሳችሁ በኋላ **ከምንም የበለጠ እንዲታወቅልን የምንፈልገው የአንድነት ድጋፍ ድርጅት ብንባልም ታማኝነታችን ለታወቁ ግለሰቦች ወይንም ለፓርቲው አመራር አባላት ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብና በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ለተቀመጡትና የኢትዮጵያን ሕዝብ ይጠቅማሉ ለምንላቸው መርሆዎች ነው።** ትሉናላችሁ፤ ግሩም ቃላት ተደርድረዋል፤ ግን እስቲ ደጋግማችሁ አንብቡትና ምን መልእክት ልታስተላልፉልን እንደፈለጋችሁ አጣሩ! መርሆዎቹ ዓላማዎች ናቸው፤ ለነዚህ ዓላማዎች መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ማን ወይ ምንድን ነው? የአንድነትን መርሆዎችና ደንቦች እንዲያስከብሩልን የመረጥናቸው ሰዎች መርሆዎቹንም ደንቦቹንም ለወጡብን ብለን ስንጮህ የስድብ ናዳ ታወርዱብናላችሁ፤ እንደሎሌዎቻችሁ በማየት አናስደፍራቸውም ትሉናላችሁ፤ ዘወር ብላችሁ ደግሞ ድጋፋችሁ ለመርሆዎቹ እንጂ **ለታወቁ ግለሰቦች ወይንም ለፓርቲው አመራር አባላት** አለመሆኑን ትነግሩናላችሁ! እነዚህ ሁሉ ሲወጡ እስቲ እባካችሁ በልዩ ጥበባችሁ ዘዴ አግኝታችሁ እንደሆነ ዓላማዎቹን ማን እንደሚያስፈጽማቸው ንገሩን፤ ቃላት መደርደር ትርጉም ያለውን ሀሳብ አያስተላልፍም።

አንድ የጥላቻ ፖሊቲካ የወለደው ጀብደኛ የመምሰል መፈክር ተወርውሮብናል፤ **በየአፍቃሬ ወያኔ ድረ ገጹ** የሚል ክስ ቀርቦብናል፤ እንደገባኝ በደብዳቤው ውስጥ ተደጋግሞ እንደሚታየው ያስተሳሰብ መዛባት የሚታይበትና ዓላማውም ጤናማ ያልሆነ አነጋገር ነው፤ አፍቃሬ ወያኔ የሆኑ ዜና ማሰረጫዎች ላይ ማውጣት አፍቃሪ ወያኔ ያደርጋል የሚል መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ ይጋብዛል፤ መጀመሪያ የዜና ማሰራጫዎቹን ባለቤቶች ከዜናው ጋር ማምታታት ትክክል አይደለም፤ የትኛውም የዜና ማሰራጫ ትክክለኛውን ዜና ወይም ዘገባ የሚያወጣ ከሆነ ልንጠቀምበት የማንችልበት ምክንያት ምንም የለም፤ ሁለተኛ አንድነት ውስጥ በተፈጠረው የአመለካከት ልዩነት ወያኔ የሚፈነጥዝ ከሆነ እኛን ሊያሳፍረን የሚገባው እንደወያኔ ድፍንና ለቅቀውት ሲወጡ ብቻ ቆሻሻውን የሚናገሩበት ድርጅት አለመሆኑ አይደለም፤ ይህ ያኮራናል እንጂ አያሳፍረንም፤ የሚያሳፍረን በድርጅታችን ውስጥ ሆነን በነጻነት ስለቆሻሻችን መናገራችን ሳይሆን ቆሻሻው ከተከሰተ በኋላ ለማፅዳት ፍላጎት አለመኖሩ ነው፤ ስለወያኔ ቆሻሻ እየተናገርን የራሳችንን ቆሻሻ በወያኔ የዜና ማሰራጫ አይውጣ ማለት በበጎ ከታየ የንግድ ሽሚያ ብቻ ይመስላል፤ ትልቁ ቁም-ነገር ለእኛ የምንፈልገውን ነጻነት ወያኔን ልንነፍገው የማይገባ መሆኑ ነው።

በመጨረሻም አመራሩን የማትደግፉ መስላችሁ ዝምአንልሞችን በመረረ ሁኔታ ማውገዛችሁ ልባችሁ የት እንዳለ በግልጽ ያመለክታል፤ ለእኔ እንደገባኝ የገንዘብ ድጋፋችሁን እንደኃይል ቆጥራችሁት ከአንድነት አመራር ጋር በማበር የእነሱን ጉልበት በማጠንከር እኛን ዜሮ የማድረግ ዓላማ አንግባችኋል፤ **የሚደረገው መሯሯጥና መፍጨርጨር ልባችንን እያደማን እንደሆነና ሙከራውም ከንቱ እንደሆነ የቡድኑን አባላት ልናስታውስ እንወዳለን** በማለት አቀዋማችሁን ገልጻችኋል፤ እንደማንም በጡንቻ የሚተማመን አምባገነን ገንዘባችሁ አቅማችሁን በትክክል ለማወቅ እንዳትችሉ አድርጓችኋል፤ ማን ለእውነት እንደቆመና የማን ሙከራ ከንቱ እንደሚሆን ጊዜው ሲመጣ እናያለን፤ እኛ የታየንን እውነት ይዘን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በገባነው ቃል ኪዳን መሠረት በነጻነት ትግላችንን እንቀጥላለን፤ እናንተና የአንድነት አመራር ከበስተጀርባችሁ የሚገፉችሁን ኃይል ተማምናችሁ ቀጥሉ፤ የአንድነት ዓላማ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከሎሌነት ለማውጣት ስለሆነ የማንም ሎሌ አንሆንም።

ለነጻነት ለመታገል የመረጠ ሰው በጡንቻ አምባገነንና በገንዘብ አምባገነን መሀከል የሚመርጠው የለውም፤ ከጅብ ዋሻ ወደጅብ ዋሻ አይገባም።

ወደፊትም ቢሆን ስለዝምአንልሞች ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ እንደማንም ሰው በሙሉ ነጻነታሁ ተጠቅማችሁ የምታዩትን ስሕተት ሁሉ ብትጠቁምን ደስ ይለናል እንጂ አይከፋንም፤ ነገር ግን የራሳችሁን ልዩ ተልእኮ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለብርቱካን ከእኛ የበለጣችሁ ተቆርቋሪ በመምሰል መመጻደቁን እንድትተውት እናሳስባችኋለን።

በዝምአንልሞች ስም መልስ እንደተሰጠ አውቃለሁ፤ ይህ ደብዳቤ የኔ የግሌ መልስ ነው፤ ለዚህ ደብዳቤ ኃላፊነቱን የምወስደው እኔ ነኝና በዚህ መንፈስ ተቀበሉት፤…ወይም ጣሉት።

አክባሪያችሁ

መስፍን ወልደ ማርያም
(**ታዋቂ ግለሰብ** ካላችሁት አንዱ!)